# ታጠቅ - ኢትዮጵያ

## ታጠቅ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ልሳን

## ልዩ መግለጫ

ታህሳስ 19 1999

## ለዴሞክራሲ ከምናደርገዉ ትግል እንዳንዘናጋ!

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በደምሙና በአጥንቱ መስዋዕትነት ከፍሎ ከዉጭ ወራሪዎችና ከዉስጥ አምባገነኖች አገሩን ሲከላከልና ከጭቆና እራሱን ለማላቀቅ ሲታገል ኖሯል:: አሁንም የዴሞክራሲያዊ መብቱን ነጥቆ፣ የምርጫ ድምጹን ሰርቆ፣ መሪዎቹን ገሎና አስሮ የተለመደዉን ጭቆና የዘረጋዉ ኢሕአዴግን በተለመደዉ ያለፍትሕ አልገዛም ባይነቱ ጭቆናዉን በመታገል ላይ ይገኛል:: ትግሉም ዘርን፣ኃይማኖትን ያልለየና ለመላ አገሪቱ ሕዝብ የእኩልነት መብትና ደህንነት የቆመ ነዉ::

በዚህም የሕዘባችን የትግል ሂደት ዉስጥ፣ ባንድ በኩል አምባገነኖች የራሳቸዉ የሕዝብ ድጋፍ ስለሌላቸዉ ከዉጭ እጁን ለዘረጋላቸዉ ሁሉ የአገራቸዉን ደህንነት እነኳ ሳይቀር አደጋ ላይ በመጣል ድጋፍን ለማግኘ ት እንደሚሞዳሞዱና የዉስጥ ተቃዉሞዎችን ለማዘናጋት ደግሞ ሌላዉን አገር አልፎ ተርፎም እንደሚተናኮሉ ተገንዝቧል:: የኢትየጵያ አምባገነኖች ካንድም ሁለቴ ይህን ሲያደርጉና አገሪቱን ከፍተኛ ችግር ላይ ሲጥሉ ታዝቧል:: የዘመኑ ምሳሌያችንም ኢሕአዴግ በሶማሊያ በተከሰተዉ የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች እንቅስቃሴን በማጉላት ለመጠቀም የተደረገዉ ሙከራ ነዉ:: አንዳንድ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራንም ለዚህ የተባባሰ ሁኔታ መፈጠር የኢሕአዴግ እጅ እንዳለበት ያስረዳሉ:: ይህ መሆኑም ሕዝባችንን አያስደንቀዉም፣ከዚህ በፊት በኤርትራ ጉዳይ ላይ ካንዴም ሁለቴ ኢሕአዴግ እንዳሳዘነዉ ሕዝባችን ያስታዉሳል:: ታዲ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ በአጥፊዉ ኢሕአዴግ ላይ እንደማትኮርና አንድነታቸዉን ጠብቀዉ የኢትዮጵያ ሕዝብን ፍላጎትና ደህንነትን የሚያስከብር አመራር መስጠት ተስኗቸዉ ሕዝባችን በኢሐአዴግ ልጓም (አጀንዳ) ተስቦ ጦርነት ዉስጥ ገብቷል::

የሕዝባችን የጋራ መለያ በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያዊነቱ ነዉና በዚህ ላይ ክንዱን ያነሳበትን፣ ዘሩን ኃይማኖቱን ሳይለይ ተዋግቶ ነፃነቱን አስከብሯል:: በአገሩ ላይ በዘር ስም ይሁን ወይ በኃይማኖት እንዲሁም በሌላ ሲነሱበትም፣ ሥረመሰረታቸዉ አገሩን ሊነጥቁ ወይ ሊያፈርሱ መሆናቸዉን ያዉቃልና ሙስሊምና ክርስቲያን ልጆቹ ባንድ ላይ ቆመዉ አገራቸዉን ተከላክለዋል (ከሶማሊያ ጋር የተደረጉት የሃያኛዉ ምዕተ ዓመት ሁለት ጦርነቶች የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎች ናቸዉ):: አገሩን ከደፈሩበት፣ ብሄራዊ ነጻነቱን ከነኩ፣ ክርስቲያን ነኝ ይበሉ ሙስሊም፣ አፍሪካዉያን ይሁኑ አዉሮፓዉያን የጋራ አገራዊ ጥቅሙንና ሕልዉናዉን ለማስከበር ባደረገዉ ተጋድሎ የኢትዮጵያ ታሪክ በክብር ተንቆጥቁጦ ይገኛል::

Tatek Ethiopia Information Centre,
PO Box 4281, London WC1N 3XX e-mail: Tatekethiopia@hotmail.com

በአሁኑ ሰዓት የኢሕአዴግ መስተዳድር የሶማሊያ የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች ጅሃድ በኢትዮጵያ ላይ አዉጅዋል፣ጠላቶቻችን በሃገር ደረጃ ፍ/ቤቱን በማገዝ በእጅ አዙር እየወጉን ነዉ፣ በድምሩም የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ተደፍሯል በማለት ከሶማሊያ የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች ጋር በተካሄደዉ ፈጣን ዉጊያ በ ፍ/ቤቶቹ ወታደራዊ ሽንፈት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህን ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች በሕዝባችን ዘንድ ይጉላላል፡፡ ለምሳሌም እዉነት የኢትዮጵያ ሕልዉና አደጋ ላይ ወድቆ ነበር ወይ? ካልወደቀ የዚህ መስተዳደር ዓላማ ምንድን ነዉ? ሕልዉናችን አደጋ ላይ ወድቆስ ከሆነ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለዚህስ ሁኔታ ተጠያቂ ማን ነዉ?ወዘተ.

በኛ በኩል ባለን መረጃና ባደረግነዉ ግምገማ መሰረት፣ በርግጥ አሳሳቢ ሁኔታዎች ቢኖሩም ይህ ጦርነት በተካሄደበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕልዉና አደጋ ላይ ወድቆ ነበር ማለት አያስችልም፡፡ ይህ ወታደራዊ ድል የሚያስገነዝበዉም የኢትዮጵያን ጦር ብቃትና ቅልጥፍናን ብቻ ሳይሆን በተለይ ባጭር ጊዜ መጠናቀቁ የኢትዮጵያን ጉልበት የሚመጥን «የፍርድ ቤቱ» ጉልበት እንዳልነበረና ስለዚህም በእዉነት የኢትዮጵያ ሉአላዊነት በአሁኑ ወይም በቅርብ ጊዜ አደጋ ላይ እንዳልወደቀ/እንደማይወድቅ ነዉ፡፡ ይህም የኢሕአዴግ ጦርነት የመቀስቀስ ስዉር ዓላማን ግልጽ ያደርገዋል፡፡ ኢሕአዴግ የራሱን ዕድሜ ለማራዘም ብቻ ያቀደዉ ጦርነት እንጂ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ባለመሆኑ የተደረገዉን ጦርነት አንደግፍም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕልዉና አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ በታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየዉ ሕዝባችን አንድነቱን ጠብቆ ይዋጋል፣ ነፃነቱን ያስጠብቃል ብለን እናምናለን፡፡ በአገራዊ ሉአላዊነቱና በነፃነቱ ላይ የመጣዉ የጋራ የሃገር ጠላት በመሆኑም በአክራሪ ክርስቲያን ስም ይሁን በሙስሊም ወይም በሌላ፣ ዘዉጌያዊ ይሁን አገር አቀፍ፣ በሌሎች ቡድኖች ወይ ሃገሮች ተደገፈ አልተደገፈ፣ አንድነቱን ጠብቆ ይከላከላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ላይ ፈጽሞ የሚያሳስብ ሁኔታ እንደሌለ የሚሚገቱ ወገኖች አሁኑኑ አገራችን አደጋ ላይ ወድቃለች ከሚሉ ወገኞች ያላነሰ መዘናጋትን እንዳይፈጥሩ እንሰጋለን፡፡ እስቲ እነዚህን አሳሳቢ የምንላቸዉን ሁኔታዎች እናስቀምጥና አንባቢ ይመዝናቸዉ፡፡

ለአገራችን አሳሳቢነትን ፈጥረዋል የምንላቸዉ አንዳንድ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

1. የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች መሪዎች ኢትዮጵያ በሶማሌ ሕዝብ የዉስጥ ጉዳይና በመሬታችን ጣልቃ ገባች በማለት አግባብ ባለዉ ክሳቸዉ ላይ እንደመወሰን ፋንታ፣ በኢትዮጵያ የሶማሌን ክልል እወስዳለሁ በማለት በኢትዮጵያ የዉስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባታቸዉ፣
2. ለዚህም ዓላማቸዉ የኢትዮጵያን መድከም ወይም መፍረስ ከሚፈልጉ አገሮችና ከኢትዮጵያ መገንጠል ፍላጎት ካላቸዉ ኃይሎች ጋር ሁሉ በማበራቸዉና በመታገዛቸዉ
3. የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች መሪዎች የሁለቱም ታላላቅ ኃይማኖቶች ቤት የሆነችዉንና በቅዱስ ቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ የተከበረ ቦታ ያላትን ቅድስት አገራችንን፣በሁለቱም ኃይማኖቶች ከራሷ ተርፋ ሌላዉን ማስተማር የምትችለዉን አገራችንን በመፈታተን ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸዉን ችግር የኃይማኖት መልክ ለመስጠት እየሞከሩ መሆናቸዉ ነዉ፡፡

እነህ አሳሳቢ ሁኔታዎች ቢሆኑም በአጽንኦት ለመግለጽ የምንፈግገዉ የተባበሩት ኢስላሚክ ፍ/ቤቶች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ጥሏል ሊያሰኝ የሚያስችል ሁለንተናዊ ጉልበትም ስለሌለዉ

የኢሕአዴግ ጦርነት ማወጅ ለአሳሳቢዉ ሁኔታ ተመጣጣኝ ምላሽ አልነበረም። ተመጣጣኝ ምላሹ የነበረዉ የኢትዮጵያን ጦር ከሶማሊያ መሳቡና የሰላም መንገዶችን መከተል ይሆን ነበር ብለን እናምናለን።

ስለዚህም በጥቅሉ የኢሕአዴግ ጦር መምዘዝ፣ ዓላማዉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከትግሉ መስመር ለማፈናቀል መሆኑ የበለጠ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ጉዳዩን በአንክሮ በመመልከት ባፋጣኝ ሕዝባችን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተመረጠ መስተዳድር በመመራት ለሚገጥመዉ የአገርና የሉአላዊነት ችግሮች እራሱ መልስ ለመስጠት ካልቻለ፣ የአገራችን ደህንነት በአምባገነን መስተዳደር በመያዣነት ተይዞ መቀጠል የበለጠ ችግሮች ዉስጥ እንደሚከተዉ በመገንዘብ የዴሞክራሲያዊዉን ትግል መጠናከር አሁንም ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ መሆን ይገባዋል። ዘላቂነት ያለዉ መፍትሔ ለአገሩም መስጠት የሚያስችለዉ መሳሪያ ይህ ብቻ ነዉ። ስለዚህም አሁንም ሕዝባችን የትግል ኢላማዉን ሳይዘናጋ በኢሕአዴግ ላይ ማነጣጠር መቀጠል አለበት እንላለን። ይህን ስንል አንዳንድ የዋሆች ከኢህአዴግ ጥላቻ ተነስተን የሚመስላቸዉ ይኖራሉ። ይህም የተንኮሉን እርቀት ባለመገንዘባቸዉ ይሆናል። እዉነትማ የኢትዮጵያ ሕልዉና አደጋ ላይ ወድቆ ቢሆን ኖሮ ከኢሕአዴግ ጠላትነት በመነሳት ለአገሩ የማይዋጋ ሰዉ ሃገር ወዳድ ሊባልም አይችልም እንላቸዋለን።

አሁን ያለዉ ሁኔታ በግራም በቀኝም ብዙ የአካባቢዉና ዓለም አቀፍ ተዋናዮችን ያሳተፈና አጀንዳዎችን ያዘለ፣ብዙ ተንኮልና ታሪካዊ በቀልንም ያካተተ፣ኃይማኖትን መሳሪያ ለማድረግ የሚሞክር፣የዘዉጌ አጸናፋዊ ፖለቲካን የጨመረ፣ አገሬዉ ብቻ ሳይሆን ቅጥረኞችም የተመለመሉበት፣ በአጠቃላይ ወታደራዊ ድሎች ሌሎች የተወሳሰቡ ቀጣይ ግጭቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉበት፣ ለአካባበቢዉም የተባባሰ ሁኔታን ሊፈጥር የሚችል ዉስብስብ ሁኔታ ነዉ። ሌሎች አገሮች ተመቻችተዉ ከድሎት የሚመሩት የዉክልና ጦርነት፣ አገራችንንም ሆነ አካባቢያችንን በድሕነት ላይ ድሕነት፣በሞት ለይ ሞትና መከራ እንዳያወርሳት ያሰጋል። የሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርአተ መንግሥት በአገራችን ባልተቋቋመበት ወቅት፣የሕዝብ ፈቃደኝነት ባልተጠየቀበት ወቅት የሚካሄዱ የአንድ ወገን አገር አቀፍ ዉሳኔዎች ዉለዉ አድረዉ አገሪቱን ቀዉስ ላይ እንደሚጥሉ የታወቀ ነዉ።ጊዜያዊ ወታደራዊ የበላይነት ብቻዉን መፍትሄ አይደለም፣ሕዝባዊ መሰረትና ፈቃደኝነት ከሌለዉ። በድጋሚ አሁንም ወደ ዴሞክራሲያዊ ትግላችን ካላተኮርን፣አንደ አንዳንድ የዋህ አገር ወዳዶች ከተዘናጋን መልሶ የአገራችንን መበታተን ሊያስከትል የሚችል፣ ዉሎ አድሮ የአገር ህልዉናን ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ዉስጥመዉደቃችን አይቀሬ ነዉ። የጊዜዉ የኢሕአዴግ የጦር የበላይነት በሶማሊያ የሽምቅ ተዋጊዎችና በሕዝባዊ ተቃዉሞ እንደሚጠመድ አያጠራጥርም። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት ጦራችን ከሶማሊያ እንዲወጣና ሌሎች የሰላም እርምጃዎችን መዉሰድ፣ ኢሕአዴግ ላይ ተጽዕኖ ከማሳደር ጀምሮ ለሰላም ዓለም አቀፍ ቅስቀሳና ጥሪ ማድረግ፣እንዲሁም ከዴሞክራት የሶማሊያ ዜጎች ጋር ሆኖ ለሰላም የጋራ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አስፈላጊና አስቸኳይም ናቸዉ።

ታጠቅ የሚከተሉት የሰላምና አገራዊ የደህንነት መንገዶችን ልንወስድ ይገባል ይላል፡-

1 በሶማሊያ ጉዳይ በሁሉም ወገን የተሰነዘረዉ የዉጭ ጣልቃ ገብነት እንዲቆም ማድረግ

2 በሶማሊያ አሁንም በሕዝብ ዘንድ ተሰሚነት ባላቸዉ ኃይሎችና በሽግግሩ መስተዳድር መሐል ያሉ ልዩነቶች በዉይይት እንዲፈቱና በሶማሊያ የሰላምና መረጋጋት በር እንዲከፈት ሁሉን ጥረት ማድረግ

3 የኢሕአዴግ መንግስት እያደር ከሚገባበት ትርምስ እራሱንም ይሁን አገራችንን ያወጣ ዘንድ ልቦና በማድረግ የታሰሩትን መሪዎቻችንን በመፍታትና ለሁሉም የሚበጀዉን የሰላምና የዕርቅ አገር አቀፍ ጉባኤ ያካሄድ ዘንድ በአገር ዉሰጥም ያለን ሆንን በዉጭ አገር የተሰማሩ ኢትዮጵያዉያን ከፍተኛ ግፊት እንድናደርግ ማድረግ

4 በሁለቱ አገሮች መሐል በዘለቄታዉ የጦርነት ሁኔታ እንዳይፈጠር ለችግሮቹ የመፍትሔ ሃሳቦች እንዲጠኑና ሕዝባችን እንዲወያይበት ጥረት ማድረግ

ወንድማችን የሶማሊያ ሕዝብ የራሱን ችግር እራሱ እንዲፈታ ሁሉም ጣልቃ ገብነት ይቁም!
በኢትዮጵያ መልካም መስተዳደር፣ በሶማሊያ ሰላም ለማምጣት እንታገል!
ለአገራዊ ሉዓላዊነትና አንድነት መተማመኛችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ብቻ ነዉና
ለዴሞክራሲ ሳንዘናጋ እንታገል!

ታጠቅ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር